ፓኖራማ ቁጥር 76

የትዝብት አድማስ

ነሐሴ 17 ቀን 2001 ዓም

## በአንድነት ላይ ቀጣይ አደጋ

ከአስራ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ሦስት ዓመተ ምህረት አንስቶ÷የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅምና የግዛት አንድነት የሚጠብቅ መንግሥት ባለመኖሩ ፤ የሀገራችን ብሩህ ተስፋ ቀስ በቀስ እየቀጨጨ በመሄድ ላይ ይገኛል ። አንድ ሀገር ልክ ለቅርጫ እንደታረደች ላም አንገቷ÷ ጎኗ ÷ እና ሌላውም የሰውነት ክፍሏ ተቋራርጦ የመገነጣጠል ሂደት ማየት በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ክስተት ሆኗል ። የሰከረ አሳ እንዳያመልጣችሁ እንደተባሉ ሁሉ÷የወቅቱን የሀገሪቱን አሳዛኝ ሁኔታ አድፍጠው በመጠባበቅ የነበሩና ያሉ ክፍሎች ዓላማቸውን ለማሳካት ሌት-ተቀን ተግተው በመስራት ላይ ናቸው ። ሌላው ወገን ደግሞ ይህን ሂደት እንደምንም ብሎ አስቁሞ ሀገሪቱን ማዳን ሲገባው ፤ አዲስ አበባ ላይ እርስ በእርሱ በመራኮት ላይ ይገኛል ። ወቅቱን እየጠበቁ ወያኔዎቹ በሚወረውሩለት አጥንት ላይ ስለሚፋጅ÷ሀገሪቱ የምትሄድበትን አቅጣጫ በቅጡ ለማየት የሚያስችለው ወገጋን ሁሉ ተደፍኖበታል ። ዛሬማ ጨርሶ የወያኔ ፖለቲካ ጨዋታ ዳር ደንበርን ከመቆራረስ አልፎ ተርፎ ÷ በመሀል ሀገር የሚገኙትንም ለም ቦታዎችንና ድልብ መሬቶችን ለባዕዳን በመሸጥ ላይ ይገኛል ። የዳር ድንበሩ ወሰን እየጠፋ መኻሉ ዳር እየሆነ ነው ። ሀገሪቱም ትላንት የተሰውሏትን ጅግኖች የረሳች በመሆኗ ዛሬ ሊወጡ የሚችሉ ጀግኖች ሊከሰቱ አልተቻላቸውም ። እንደ ድመት የራሱን ልጆች የሚበላ ኅብረተስብ ደግሞ ፡-

**“አባቴ አልረገመኝ ÷እያቴ አልረገመኝ ÷ ይህ አርበኛ ማጣት ዘንድሮም ደገመኝ ”**

እያለ ሙሾ ቢደረደር የሚደርስለት አላገኝም ። መድህኒቱን ፈጥነው ካላገኙ በሽታው ማጥቃቱን ይቀጥላል ። በተለይማ በሽታውና መድህኒቱ በአንድ በርኖስ ውስጥ ከተሸፈኑ እነርሱን በመለያየት ተውሳኩን አውጥቶ በፈውሱ ለማጥቃት አይቻልም።

ከሱዳን ጋር የሚያዋስኑት የሀገሪቱ ምዕራባዊ ለም መሬቶች÷ ከደናቸውና አዝርዕታቸው÷ ከአራዊቱና እንስሳቱ ÷ ከአዕዋፋቱና ዕጽዋቱ ጋር በሱዳን መንግሥት ወታደሮች ወረራ እየተካሄደባቸው ይገኛል ። በአካባቢው የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን ዜጎች ሳይቀሩ

ሕልውናቸው ለማያቋርጡ አደጋዎች እየተጋለጡ ናቸው ። በቆዳ ስፋት በአፍሪካ ውስጥ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ሱዳን፥ የራሱ መሬት አልበቃው ብሎ ፥ የኢትዮጵያን ለም መሬቶች ለመውሰድ የነበረውን የቆየ ዕቅድ በተግባር ለመለወጥ ከአሁን የበለጠ ምቹ ጊዜ አልመኖሩን በትክክል ተረድቶታል ። የጥንቱን የጧቱን ታሪክ ለጊዜውም ቢሆን ወደኋላ አቆይተን ፥ ከዛሬ 120 ዓመታት ወዲህ ማለትም፥ ከዮሐንስ አራተኛ ዘመነ መንግሥት ወዲህ ያለውን የሱዳንን የሀገራችንን መሬት ፍለጋ ተንኮል ብቻ እንኳን ብናጤን ፥ በማስረጃ የተደገፉ ወረራዎችን መጥቀስ እንችላለን ። ሁሉም የሱዳን ወረራዎች በዘመኑ በነበሩ መሪዎች ድል ተመትተዋል። እስከ ወያኔ ወደሥልጣን መምጣት ድረስ ሱዳንን የሚያዋስኑት የኢትዮጵያ ምዕራብ ወሰኖች እንደተከበሩ ነበር ።የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም ወጣቱ ትውልድ ሊረዳው የሚገባ ታሪካዊ ሀቅ ቢኖር፥ ልክ የዛሬ 120 ዓመት የሱዳንን ወረራ ለመመለስ በተደረገው ጦርነት ዘመቻውን በመምራት መተማ-ጋላባት ላይ የተሰውት ከትግራይ ክፍለ ሀገር የበቀሉት ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት አራተኛ የነበሩ መሆናቸውና፥ አሁን ደግሞ የኢትዮጵያን የምዕራብ ግዛት ለዛሬዎቹ ሱዳኖች የሚያስረክቡት በኢትዮጵያዊነቱ በሚኮራው በትግራይ ሕዝብ ስም ሥልጣን ላይ የወጡት ከሃድያን የወያኔ ግለሰቦች መሆናቸው ነው ። ይህን የታሪክ ምፀት፥ የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በጠቅላላው ፥ የትግራይ ሕዝብ ደግሞ በተለይ እንዲገነዘበው ጥሪያችንን እናስተላልፋለን ። እኛም ይህንን የዛሬውን የትዝብት አድማስ ሐተታችንን ፥ በአስራ ስምንት መቶ ሰማኒያ አንድ ዓ ም የሱዳንን ወረራ ለመመከት በተደረገው ጦርነት መተማ--ገላባት ላይ ደሙን ላፈሰሰው ፥ አጥንቱን ለከሰከሰው ጀግና ሰማዕት የኢትዮጵያ ጦር በመታሰቢያነት እናቀርባለን። ይህንን መታሰቢያ፥ ለዝክረ-ታሪክና ለጀግኖች ማስታዎሻም ብቻ ሳይሆን ፥ የእነርሱን ጦርና ጋሻ በማንሳት ለሀገራችን ነፃነትና ለግዛት ሉዓላዊነት ቀናዒ መሆናችንን ለማረጋገጥም ጭምር ነው ። ጊዜው ሲመጣም ያለጥርጥር የወያኔ ቡድኖች ዛሬ ለሱዳን ያስረከቡትን የኢትዮጵያ መሬት የኢትዮጵያ ሕዝብ ያስመልሳል።

በደቡብ ምዕራብ ሱዳን የሚገኘው የዳርፉር ሕዝብ ከአለፉት በርካታ ዓመታት ጀምሮ የደረሰበትን አሰቃቂ ሁኔታ መላው ዓለም የተረዳውና ብዙም የተባለለት ስለሆነ ፥ ስለዚህ ጉዳይ በተጨማሪ የምንለው ላይኖረን ይችላል ።ይህ የወቅቱ የሱዳን መንግሥት ግን የራሱን ሕዝብ ችግር መፍታት እያቃተው ፥ በሀገራችን በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርገውን ጥቃት፥ እንዲሁም ወሰን እየጣሰ በመግባትም በዜጎቻችን ላይ የሚያደርሰውን በደል በአርምሞ መመልከት አንችልም ። እርግጥ በወቅቱ በኢትዮጵያ ግዛት ሥልጣን ላይ ያለው ከሃዲ ቡድን ሙሉ ትብብርና ስምምነት ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፥ሱዳን በሀገራችን ውስጥ ገብቶ ወንጀል መፈፀሙ በኃላፊነት ከመጠየቅ እንደማያድነው ሊገነዘበው ይገባል ። ይህ ሁኔታ፥ ምናልባት ወያኔ በሥልጣን ላይ እያለ ምንም የሚያመጣው አንደምታ ላይኖር

ይችል ይሆናል ። ነግ ተነገ ወዲያ ግን ፥ በወያኔ ከርሰ-መቀብር ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱን መንግሥት ሲመሰርት የሀገራችንን የግዛት አንድነትና የነፃነት ልዕልና ለማስከበር ይገደዳል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱ የሆነ መንግሥት ሲመሰረት ማለት፥ ያ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ ፥ ብሄራዊና ሀገር ወዳድ መሆኑን በተግባር እየገለፀ ኢትዮጵያዊነቱን ሲያስመሰክር ብቻ ይሆናል ማለት ነው ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ታዲያ ዛሬ ከማንምና ከምንም በላይ የሚያሻው ኢትዮጵያዊ መንግሥት እንደሆነ ከልብ ያምናል ። ኢትዮጵያዊ መንግሥት ያስፈልገዋል ሲባል ፥ በዜግነቱና በትውልዱ ብቻ ሳይሆን ፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለሀገሪቱ ብሔራዊ ልዕልና የቆመና ይህንንም ተግባር የሚፈጽም እንጅ ፥እንደ ወያኔ ቡድኖች ሀገር ሻጭና ለኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ያጎበደደ ማለት አይደለም ። ግብፅ ዛሬ በሀገራችን ላይ ፉከራዋን ስታጧጧፍ እሰየው የሚላት መንግሥት ሳይሆን፥ ይህን አደጋ ሊከላከል ከሕዝብ ጋር ሆኖ የሚዘጋጅ መንግሥት ማለት ነው ። ከባድ ብሔራዊ ችግር ሲመጣም በግንባር ቀደም የሚሰዋ መሪ እንጅ ፥ በቀውጢ ሰዓት ሀገሪቱን ለመከራ አጋልጦ የሚሸሽ መሪ በታሪክም ይሁን በትውልድ ከበሬታና አስመስጋኝ ታሪክ አይኖረውም ። አንዱ የሰራውን ሌላው ማጥፋትም ሊያስመሰግን አይችልም ። የዛሬ አስራ ዘጠኝ ዓመት፥በፈታኝ ወቅት ሀገሩንና ሕዝቡን ከድቶ የሸሸው መንግሥቱ ኃ/ ማርያም በሥልጣን ዘመኑ ፥ አፄ ኃይለ ሥላሴን በምፀት አነጋገር ፥ “ ሕዝቡን ጥለው የሸሹ የታሪክ መሳቂያ ንጉሥ ” ማለቱን ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ በንቀት ትዝብት ይመለከተዋል ።መለስና ጓደኞቹም በተመሳሳይ የታሪክ ሂደት እንደሚጓዙ ሊያሳያቸው ቀርቶ ደፍሮ ሊነግራቸው የሚችል ወደጅ ዘምድ አላጋጠማቸውም ። ይህ ታዲያ ዞሮ ዞሮ የሚጎዳው፥ሀገሪቱን እንደሚሆን ፥አርቆ አሳቢ የሆነ ዜጋ ሁሉ ይገነዘበዋል ። ለወንጀለኞች እንደ ተግባራቸው ብያኔ የሚሰጠው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን ባይዘነጋም ፥ ሀገር አጥፊዎቹ አጥፍተው ሲጠፉ በዚህ ሂደት ፥መተኪያ የማይገኝላቸው ብዙ ዜጎች ሀገሪቱ እንደምታጣ ደግሞ የታወቀ ነው።

የሀገሪቱ ምዕራብ ግዛት ፥ ቀስ በቀስ ወያኔ ለሱዳን እያስረከበ መሆኑን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቅርብ እየተከታተለ እያለ ፥በምሥራቅ በኩል ተንጣልሎ የሚገኘው የውጋዴን መሬት ዛሬ በወያኔ ፥ ዉሎ አድሮ ጊዜውን እየጠበቀ በሚፈነዳ ቦምብ እየታጠረ ነው ። ይህ የሀገሪቱ ምሥራቃዊ አውራጃ ፥ እጅግ ሰፊ ከመሆኑ አልፎ ተርፎ ፥ ሰላምና ፀጥታ ሰፍኖ ፥ የሀገሪቱ የግዛት አንድነትና ብሔራዊ ልዕልና በአስተማማኝ ሁኔታ ከተረጋገጠላት ብሎም ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተረጋጋ ሁኔታ ተፈጥሮለት ወደ ልማቱ የሚያመራበት ዕድል ካገኘ ፥ የውጋዴን መሬት የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ጀርባ አጥንት እንደሚሆን ፥ በሙያው መስክ የተካኑ ጠበብቶች ያረጋግጣሉ ። ከኢትዮጵያ ተራሮችና

ረባዳ መሬቶች እየተነሳ የሀገሪቱን ለም አፍርና ማዕዳን በገፍ እያግበሰበሰ የውጋዴንን ግዛት ሰንጥቆ ወደ ሶማሊያ የሚገባው ዋቢ ሸበሌና ሌሎች ግልገል መጋቢ ጅረቶች ጠቃሚነታቸው ለነዋሪው ሕዝብ ሳይሆን ለሶማሊያ ነው ። ሶማሊያ በዋቢ ሸበሌ ብቻ በርሻ የተመሰረተ የኢኮኖሚ ግንባታ እንደምታደርግ የሚያውቅ ያውቀዋል ። በታሪክ፥ የውጋዴንን ግዛት ለማስቆረስ የተለያዩ ጦርነቶች እንደተደረጉ መዘርዘር አይኖርብንም ። ጠቅላላ የሀገሪቱን ነፃነት ለመግፈፍም ባዕዳን የምሥራቁን ጠርፍ ጥሰው ሲገቡ ውጋዴንን የወራሪው ጦር ማከማቻና የወታደራዊ ስልታችው መቀነባበሪያ ሲያደርጉት ቆይተዋል። ዛሬ፥ የውጋዴን ነፃ አውጭ ድርጅት የሚባል ታጣቂ ኃይል በአከባቢው በመንቀሳቀስ ላይ መገኘቱ ስውር አይደለም ። በዚህ አከባቢም የወያኔ ጦር ብዙ ግፍ መፈፀሙም የሚታወቅ ነው ። ይህን የኢትዮጵያን ኅልውና ለማጥፋት የሚያንዣብበውን ተጨማሪ አደጋ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ አውቆ ፥ የዉጋዴን ግዛት፥ የነገው ዳርፉር ከመሆን እንዲድን፥አስፈላጊውን የመከላካያ ርምጃ እንዲወስድ ጥሪያችንን ለእርሱ ለባለቤቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በቀጥታ እናስተላልፋለን ። ይህንን የምናደርገው ፥እንዲህ ብለን ነበር፥ ሰሚ አጥተን ነው እንጅ በሚል ግብዝነት ለከንቱ ርካታ ሳይሆን ፥የሚገባውን ተግባራዊ ርምጃ እያደረግንም ጭምር ነው ። የሁሉም መሠረታዊ ችግር የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ መሆኑን ስለምንረዳ ፥ በቅደሚያና በዋና ደረጃ ፀረ ወያኔ ትግላችን ይፋፋም እንላለን ። የወያኔ አገዛዝ ችግሮችን መቅረፍ ሳይሆን ፥ ወደባሰ አደጋ እያስኬዳቸው ስለሆነ ፥ የሀገራችንን ህልውና ለመጠበቅ ፥ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ/ት የዜግነት ኃላፊነትም ግዴታም ያለበት መሆኑን ይዘነገዋል ብለን አንገምትም። ሀገራችን ከተቃጡባት ተከታታይ አደጋዎች የመከላከሉ ተግባር የሁሉም ዜጋ መሆኑን ለምንታገልለት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለማስታወስ ባነቃጣም ቅሉ፥ ሀገራችንን ከወያኔ ጥፋት ለማዳን ጥሪያችንን በተደጋጋሚ እናስተላልፋለን።

ሀገር አድን ትግላችን ይጠናከር!!